# የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ

# የትምሕርት ርትዕ እና ውጤታማነት ማዕከል

## የአርሊንግተን የህዝብ ት/ቤት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች መርሐ ግብር ምዘና

የመጨረሻ ሪፖርት

እ.አ.አ መስከረም 18/2012

ባርባራ ዲ. አኮስታ፣ ከፍተኛ የምርምር ሳይንቲስት

ሎቲ ማርኩዞ፣ ከፍተኛ የምርምር ተባባሪ

ክሪስቴን ኮኖርስ፣ የምርምር ረዳት

ሻርሊን ሪቬራ፣ ዋና ተመራማሪ እና ዋና ዳይሬክተር

የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የትምሕርት ርትዕ እና ውጤታማነት ማዕከል

የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የትምሕርት ርትዕ እና ውጤታማነት ማዕከል ተልዕኮ ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ደረጃን ይጎናጸፉ ዘንድ የትምህርት መዋቅርን ማሳደግ ነው። «George Washington Univesity Center for Equity and Excellence» (በእንግሊዘኛ ምጽሃረ-ቃሉ GW-CEEE) ፖሊሲ እና ተግባራዊ ምርምርን ያካሂዳል፣ የመርሐ ግብር ምዘናን ዲዛይን ያደርጋል ፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ እናም በክልል የትምሕርት ኤጀንሲዎች፣ በትምህርት ወረዳዎች፣ ፋውንዴሽኖች እና ፌደራል ኤጀንሲዎች ውስጥ ለሚገኙ ደንበኞች የሙያ ማሳደጊያ እና ቴክኒካዊ ዕርዳታን ይሰጣል።


GW-CEEE

የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የትምሕርት ርትዕ እና ውጤታማነት ማዕከል

www.ceee.gwu.edu

800.925.3223

## ምስጋና

ለዚህ ምዘና መረጃና አስተያየታቸውን የሰጡንን አርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤት (APS) የሚገኙ በርካታ ግለሰቦች ማመስገን እንፈልጋለን። ሱፐር ኢንቴንደንት ፓትሪክ መርፊ፣ የ APS ት/ቤት ቦርድ አባላት እና «ESOL/HILT» የዜጎች አማካሪ ኮሚቴ የአስተዳደር፣ የማማከር አገልግሎትና እና ድጋፍ ስለሰጡን። የመምሪያውን እና የት/ቤቱን አመራሮች፣ መምህራን፣ ወላጆች እና የባለሁለት ቋንቋ ቤተሰብ ሐብት ረዳቶችን በዚህ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች (ELL) አመራር ቡድን ላይ ስለተሳተፉና በመነሻ ፍላጎት ግምገማ ላይ ያበረከቱትን አስተዋፅኦ እናደንቃለን። ለርዕሰ መምህራን፣ መምህራንና ለባለሁለት ቋንቋ ቤተሰብ ሐብት ረዳቶች፣ HILT ሐብት ረዳቶች፣ ጋይዳንስና መማክርቶች፣ እና ለምሪታዊ ረዳቶችም ገምጋሚዎችን ወደ ትምህርት ቤታቸውና ወደ ክፍሎቻቸው በመጋበዝ እና በቃለ-መጠይቆች፣ በቡድን ተኮር ውይይቶች፣ በክፍል ማሳያዎች እና ዳሰሳዎች ላይ በመሳተፋቸው ልዩ ምስጋና እናቀርባለን። እንዲሁም ምስጋናችንን በቡድን ተኮር ውይይቶች ውስጥ ለተሳተፉ ወላጆች እና ተርጓሚዎች እናቀርባለን።

ለመርሐግብር ግምገማ ኮሚቴም በበላይ ቁጥጥር፣ በዕቅድ ማውጣት፣ በመረጃ ስብሰባ እና ጥልቅ ጥናት እንዲሁም ምዘናው እንዲሳካ ላደረጉት የግብዓት ድጋፍ አድናቆታችን በተጨማሪም  ይድረስ፦

- ለሊሳ ስቴንግል፣ የግምገማ ረዳት ዳይሬክተር
- ሬጂና ቫን ሆርን፣ የግምገማ ስፔሻሊስት
- ፌይዝ ታባታባይ፣ የ «ESOL/HILT» ኃላፊ
- ዳን ሆዘር፣ የ «ESOL/HILT» መረጃ ስፔሻሊስት
- ሮብን ሊተን-ተጃዳ፣ ሁለተኛ የ«ESOL/HILT» ስፔሻሊስት
- ናንሲ ቤልቸር፣ የመጀመሪያ ደረጃ «ESOL/HILT» ስፔሻሊስት
- ፍራንችስካ ራሊ-ማክዶነል ፣ የ «ESOL/HILT» ልዩ ፕሮጀክቶች ስፔሻሊስት
- ኤሚ ራሚሬዝ ፣ የአስተዳደር ረዳት

ሌሎች አስተዋፅኦ ያደረጉ የ «APS» ሰራተኞች የመመሪያ ረዳት ሱፐርኢንቴንደንት (ተቆጣጣሪ) ማርጋሬት ጊልሁሊ፣ የመረጃ አገልግሎት ዳይሬክተር ሳላህ ኬልፋዊ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ-ጥበብ ኃላፊ ፓውላ ላሚና፣ የሒሳብ ኃላፊ ማርጋሬት ቹንግ፣ ቅድመ-ልጅነት እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ዳይሬክተር ሚሼል ፒካርድ፣ የሳይንስ «HILT» ስፔሻሊስት ጄኔፈር ፖዌል፣ የሒሳብ HILT ስፔሻሊስት ማሪዮላ አጉዊላር፣ የገቢ የመጀመሪያ ደረጃ ESOL/HILT ስፔሻሊስት ሊንዳ ስሚዝ፣ የትምህርት ማቋረጥ መከላከል የስራ ሐይል ሱዛን ስዊንድማን፣ የድርጅት መፍትሔ ፖል ቬሊት፣ ጄሚካ ጆንስ እና ራጅ አዱሱሚሊ እና የ ESOL/HILT አስተዳደር ሠራተኞች ማርሻ ሞትሺርድ፣ ኦድሬይ ቻን እና ሲንዲ ዋርከንቲን ለእነዚህ ሁሉ አድናቆታችንን እንገልጻለን።

በመጨረሻም በመረጃ ስብስባ፣ ግምገማ እና ሪፖርት ዝግጅት ላይ ድጋፍ ያደረጉትን የሚከተሉትን የ «GW-CEEE» ሠራተኞች ማመስገን እንፈልጋለን፡ ብሪያና ባይራክታር፣ ሻርለት ብሌን፣ ጃኔት ብራውን፣ ጄኔፈር ማክክሬዲ፣ ማርሊን ሙርሂድ፣ ማርጆሪ ሮዝንበርግ፣ ራያን ታይለር፣ እና ሮሻውን ታይሰን።

ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አላማ የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤትን (APS) ቦርድ፣ ሱፐርኢንቴንደንት፣ ለ «ESOL/HILT» ኃላፊ የሆኑ አስተዳደሮች እና ሌሎችን የወደፊት መርሐግብር ውሳኔዎችን በማሳለፍ ረገድ አገልግሎቶቹ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን (ELLs) ፍላጎት ማሟላቱን ለማረጋገጥ እንዲችሉ የተሟላ የመርሐ ግብር ምዘና ለመስጠት ነው።

የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የትምሕርት ርትዕ እና ውጤታማነት ማዕከል (GW-CEEE) የ «ELLs» የተማሪዎች ውጤታማነትን በተመለከተ አምስት ጥያቄዎችን መዝኗል። (እነሱም፣ ለግዛት መልቀቂያ ፈተና ብቁ ለመሆን የሚፈጀውን ጊዜ፤ በ«LEP» ሁኔታ ውስጥ የመቆያ ጊዜ፤ ሒሳብና ንባብ «SOL» ላይ ያለን ስኬት መድረሻ ክፍተት መዝጋት ፤ በከፍተኛ ትምህርታዊ ስራዎች ላይ የመመዝገቢያ እና የማለፊያ ውጤት፤ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ት ማጠናቀቂያ ውጤት ናቸው)። በተጨማሪም መዛኞቹ የ «APS» ፖሊሲዎች፣ ልምዶች እና የአሰራር ሒደቶች ELLsን እንዴት እንደሚደግፍ መርምረዋል ሀ) የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃታቸውን በሚያሳድጉበት ሒደት ፤ እና ለ) ከመርሐ ግብሩ በሚወጡበት ጊዜ እና ወደ መደበኛ ክፍል ለተገቢው መመሪያ ወደሚተላለፉበት ጊዜ። በተጨማሪም ይህ ድጋፍ እስከየትኛው ወሰን እንደሚደረግ ይገመግማሉ።

የተማሪዎች ውጤት መረጃ የሚዘጋጀው በዕቅድ እና ግምገማ እና እንግሊዝኛ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች/ ከፍተኛ መጠን የቋንቋ ሥልጠና (ESOL/HILT) ቢሮ ነው። በተጨማሪም የ «GW-CEEE» ገምጋሚዎች ለእያንዳንዳቸው የውጤታማነትን ማጎልበት የምስጋና ዘዴ (Promoting Excellence Appraisal System (PEAS)) ሰባቱም ጎኖች፤ መመሪያዊ መርሐ ግብር ንድፍ፣ ትዕዛዛዊ የመርሐ ግብር ትግበራ፣ አመራር፣ ሠራተኞች፣ ሙያዊ እድገት፣ ግምገማ እና ተጠያቂነት፣ እና የወላጆችና የማሕበረሰብ ተደራሽነት መረጃዎችን ሰብስበው ገምግመዋል። እነዚህ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሲሆን እነዚህም የ «APS» መምሪያ ቢሮዎች፣ የት/ቤት አስተዳደሮች፣ «ESOL/HILT» መምህራን፣ ይዘት መምህራን፣ የባለሁለት ቋንቋ ቤተሰብ ሐብት ረዳቶች፣ «HILT» ሐብት አማካሪዎች፣ ቤተሰቦች እና ተማሪዎችን ያጠቃልላል። በግኝቶቹ መሰረት «GW-CEEE» ድርጅቱን፣ አስተዳደሩን እና ለውስን የእንግሊዝኛ ብቃት (LEP) ተማሪዎች አገልግሎት የመስጠት ሒደቱን ለማሻሻል ይረዳ ዘንድ አስተያየቶቹን አስቀምጧል።

ሠንጠረዥ 1 ለተማሪዎች ውጤታማነትና ለእያንዳንዳቸው ሰባቱም የ «PEAS» አሰራር ጎኖች ጥንካሬያቸውንና እና መሻሻል የሚያስፈልጋቸውን አካባቢዎች አስቀምጧል።

ሠንጠረዥ 1. የጥንካሬዎችና እና መሻሻል የሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች ማጠቃለያ

| የ «PEAS» ይዘት | ጠንካራ ጎኖች | መሻሻል ያለባቸው አካባቢዎች |
| --- | --- | --- |
| የተማሪዎች ውጤታማነት | • በርካታ የ «ELLs» እና የቀድሞ «ELLs» ተማሪዎች ንባብ እና ሒሳብ «SOL» ላይ ያለውን የክፍተት መሙላት ውጤታማነትን በተመለከተ መሻሻል አሳይተዋል።<br>• አንድ ጊዜ የከፍተኛ ደረጃ ብቃት ላይ ከደረሱ፣ ሁለተኛ ደረጃ ላይ «APS» የገቡ የ«ELLs» ተማሪዎች ከሌሎች የ «LEP» ታሪክ ከሌላቸው ተማሪዎች ይልቅ በከፍተኛ ውጤት ይመዘገባሉ። | • ግማሽ የሚሆኑት የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች ከስድስት አመታት ለሚበልጥ ጊዜ «LEP» ደረጃ ላይ እንዲቆዩ ተደርጓል።<br>• በ2008 እ.ኤ.አ ደረጃ 3 ላይ የነበሩ የሁለተኛ ደረጃ «ELLs» ተማሪዎች በንባብና በሒሳብ «SOL» ዝግ ያለ ዕድገት አሳይተዋል።<br>• የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ «APS» ከገቡ የ «ELLs» ተማሪዎች ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ ለላቀ |

| | | |
|---|---|---|
| | | የትምህርት ስራ የተመዘገቡት።<br>• «APS» ውስጥ ካሉ የ «LEP» ያለፉ የትምህርት ማስረጃ ካላቸው ተማሪዎች ይልቅ ምንም የ «LEP» ያለፉ የትምህርት ማስረጃ የሌላቸው ተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የማጠናቀቅ ዝንባሌ አላቸው። |
| መመሪያዊ መርሐ ግብር ንድፍ | • «ELLs»ን የማስተማሪያ ዘዴዎች ጥናት ላይ መሰረት ያደረጉ ናቸው።<br>• የመምሪያው «ESOL/HILT» ክፍል የቋንቋ ጥበብና ይዘታቸው ከ«WIDA» ደረጃዎች እና «SOLs» ጋር የሚዛመድ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የትምህርት መርሐግብር መመሪያዎች አሳድጓል።<br>• «APS» ለሂስፓኒክ እና በቋንቋ ደከም ለሚሉ ተማሪዎች የትምህርት ማቋረጥ ቁጥር ለመቀነስ እርምጃ እየወሰደ ነው። | • የ «ESOL/HILT» አገልግሎቶች ከተለያዩ የ«APS» ትምሕርት ቤቶች ወይም የክፍል ደረጃዎች ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት አይታዘዝም። |
| ትዕዛዛዊ የመርሐ ግብር ትግበራ | • «ELLs»ን ያገለገሉ መምህራን በበርካታ የትምህርት ጥራት መመዘኛዎች ላይ በአንጻሩ ከፍ ያለ ውጤት ያገኛሉ። | • «ELLs»ን የሚያገለግሉ መምህራን መመሪያዎችን ለተማሪዎች ምን ያህል ግልጽ ማድረግ ላይ ይለያያሉ።<br>• የእንግሊዝኛ ቋንቋ መመሪያ «ELLs» ከክፍል ደረጃቸው የሚጠበቅባቸውን ውጤት እንዲያገኙ ለመደገፍ ትምህርታዊ ቋንቋ ላይ በበቂ ሁኔታ ያተኮረ አይደለም።<br>• የመጀመሪያ ደረጃ የንባብ መመሪያ የ«ELLs»ን ፍላጎት በቋሚነት አያሚላም።<br>• «APS» የትምህርት ክፍሎችን የሚያጠቃልል የተመረጠ ልምድን የሚከተል የተቀናጁ የማስተማር ዘዴዎች የሉትም። |
| አመራር | • የ«APS» አላማ፣ ተልዕኮ እና ግብ የ«ELLs»ን ከፍተኛ ተስፋ በውስጣቸው የያዙና የሚያንጸባርቁ ናቸው።<br>• የየመምሪያ ቢሮው አስተማሪዎች «ELLs»ን ለማስተማር ኃላፊነት ይጋራሉ። | • «ELLs»ን የማስተማር ስራ ሁልጊዜ አትኩሮት የተደረገበት፣ ቀጣይነት ያለው እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ እና ከትምህርት ቤቶች ጋር የተቀናጀ አይደለም። |

| | | |
|---|---|---|
| | • አስተማሪዎች፣ ወላጆች እና ተማሪዎች አብዛኞቹን ት/ቤቶች የሚገልጹቸው ልዩነትን በመልካም አቀባበል የሚቀበሉ በሚል ነው። | |
| ሠራተኞች | • ከመመሪያ ሰራተኞች በተጨማሪ መምሪያው «ELLs»ን እና ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ የተለያዩ ቁልፍ ቦታዎችን ፈጥሯል። | • ትምህርት ቤቶች የሁሉንም «ELLs» ቡድን ፍላጎት ለማሟላት በቂ ምሪት ሰጪ ሰራተኛ ብዛት ያንሳቸዋል።<br>• በመደበኛው የትምህርት ዘርፍ ያገለገሉ አንዳንድ መምህራንም ቢሆኑ የእነሱን ፍላጎት ለማሟላት ልምድ ያንሳቸዋል።<br>• አንዳንድ የ«ESOL/HILT» መምህራንም ቢሆኑ በሚያስተምሩባቸው ትምህርቶች ይዘት ላይ የልምድ ማነስ አለባቸው። |
| ሙያዊ እድገት | • «APS» ሁሉንም የ«ELLs» አስተማሪዎች ለእነዚህ ተማሪዎች የሚጠቅመውን የተመረጠ ልምድ ተግባራዊ እንዲያደርጉ በማዘጋጀት ለውጥ እያሳየ ነው። | • መምሪያው ለ«ELLs» የትዕዛዝ ለውጦች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የተደራጀ ዘዴ የለውም። |
| ግምገማ እና ተጠያቂነት | • «APS» ለ«ELLs» መርሐ ግብሩ በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሔድ የአሰራር ዘዴን ይፈጽማል። | • መምሪያው ለ«ELLs» የትዕዛዝ መርሐግብሮች ጥራት የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችን ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል የተደራጀ አሰራር የለውም።<br>• በአሁኑ ወቅት ያሉ የተማሪ መረጃ ዘዴዎች የ«ELL» ተማሪዎችን ለውጥ በሚገባ ለመቆጣጠር አቅም የለውም። |
| የወላጆችና የማሕበረሰብ ተደራሽነት | • «APS» ለ«ELLs» ቤተሰቦች በሚገባ የጎለበተ የወላጆችና የማሕበረሰብ ተደራሽነት መርሐ ግብር አለው። | • ሁሉም ወላጆች አይደሉም የሥልጠና እና ድጋፍ አገልግሎቶች መኖራቸውንና ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ የሚያውቁት። |

አስተያየቶች

በዚህ ምዘና ግኝቶች መሰረት አራት ወሳኝ ጉዳዮችን በተመለከተ ለውጥ ያስፈልጋል፦

(ሀ) ለ«*ELLs*» ተማሪዎች የመመሪያ መርሐ ግብር ጥራት ት/ቤት ተኮር ተጠያቂነትን ማሳደግ፤

*(ለ) የሁሉም «ELLs» ተማሪዎች ፍላጎት መሟላቱን ለማረጋገጥ የመርሐ ግብር ንድፍን ማሳደግ*

*(ሐ) ለሁሉም የ «ELLs» አስተማሪዎች ቀጣይነት ያለው በስራ የታነጸ ሙያዊ ዕድገትን ማጎልበት፤ እና*

*(መ) የ«ELLs» መመሪያዊ እና መርሐ ግብራዊ ውሳኔዎችን ለመደገፍ እንዲቻል ትርጉም ያላቸውን መረጃዎች መሟላታቸውን ማሻሻል። አስተያየቶቹ የተቀናጁት በተለያዩ የ«PEAS» ጎኖች ዙርያ መሻሻል ያለባቸውን አካባቢዎች ለማሳየት ነው። እነዚህም ከዚህ በታች ተጠቃለዋል እናም በሪፖርቱ የአስተያየት ክፍል ተገልጸዋል።*

*ለ«ELLs» ተማሪዎች የመመሪያ መርሐ ግብር ጥራት ት/ቤት ተኮር ተጠያቂነትን ማሳደግ።*

(1) ለ«ELLs» ተማሪዎች የመመሪያ መርሐግብር ጥራት የት/ቤት መሪዎችን ተጠያቂ ማድረግ።
(2) በት/ቤቱ የሚሰጡትን እያንዳንዳቸውን አገልግሎቶች የተለያዩ የ «ELLs» ቡድኖችን ፍላጎት እንዲያሟሉ አድርጎ ማቀድ።
(3) በ «ESOL/HILT/HILTEX» እና በመደበኛ ትምሕርት መምህራን መካከል ያለውን ቅንጅት ማጠንከር።

*የሁሉም «ELLs» ተማሪዎች ፍላጎት መሟላቱን ለማረጋገጥ የመርሐ ግብር ንድፍን ማሳደግ።*

(1) የ«ELLs»ን ፍላጎት ለመደገፍ ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት ንድፍ ማቅረብ።
(2) «ELLs»ን በ«LEP» ደረጃ 5 ለመምራት እና ለመደገፍ የሚመለከታቸውን ሰራተኞች መመደብ።
(3) መምህራን እንግሊዝኛን በግልጽ እንዲያስተምሩ መመሪያዎችንና የሚጠበቁ ውጤቶችን ማጠንከር።
(4) ለ «ELLs» ጭብጥን መሰረት ያደረገ የንባብ መመሪያ አቀራረብን ማደስ።
(5) ሁለተኛ ደረጃ «ELLs»ን በከፍተኛ የትምህርት ስራዎች ላይ እንዲመዘገቡና ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችንና ልምዶችን ማጎልበት።

*ለ«ELLs» ምላሽ የሚሆን መመሪያዊ ልምዶችን ለመደገፍ ቀጣይነት ያለው በስራ የታነጸ ሙያዊ ዕድገትን በማጎልበት ለሁሉም የ «ELLs» አስተማሪዎች ድጋፍን ተግባራዊ ማድረግ ።*

(1) ለሁሉም የ «ELLs» መምህራን ዘላቂነት ያለውና የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት የሚችል ሙያዊ እድገትን ማረጋገጥ።
(2) የሙያዊ ዕድገትን ውጤታማነትን መቆጣጠሪያና መመዘኛ ዘዴዎችን ማጎልበት።

*የ«ELLs» መመሪያዊ እና መርሐግብራዊ ውሳኔዎችን ለመደገፍ እንዲቻል ትርጉም ያላቸውን መረጃዎች መሟላታቸውን ማሻሻል።*

(1) አስተማሪዎች «*ELLs*» በመረጃ የተደገፈ መመሪያዊ ውሳኔዎችን ማሳለፍ እንዲችሉ የተማሪ መረጃ ዘዴን የማሻሻል ጥረቶችን መቀጠል።
(2) «ELLs» ላይ ሕዝብ ነክ የእንግሊዝኛ ብቃት እና ደረጃ መረጃዎችን ተዘጋጅተው እንዲገኙ ማድረግ።